## የፖለቲካ ፓርቲዎች የቃል ኪዳን ሰነድ ለማስፈጸም የወጣ የስነ ስርዓት ደንብ

### ምዕራፍ አንድ

### 1. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

#### 1.1 አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የስነ ስርዓት ደንብ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

#### 1.2 ደንቡን ያወጣው

የፖለቲካ ፓርቲዎች መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ.ም በፈረሙት የቃል ኪዳን ሰነድ አንቀጽ 17 (2) መሰረት ፓርቲዎቹ ያቋቋሙት የጋራ ምክር ቤት የተባለው ተቋም ነው፡፡

#### 1.3. ትርጓሜ

1.3.1 ሰነድ ማለት የፖለቲካ ፓርቲዎች መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ.ም የፈረሙት የቃል ኪዳን ሰነድ ማለት ነው

1.3.2 የጋራ ም/ቤት ማለት በቃል ኪዳን ሰነዱ ክፍል 3 አንቀጽ 14 የተቋቋመው የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ማለት ነው፡፡

1.3.3 ሰብሳቢ ማለት በሰነዱ አንቀጽ 14.4 መሰረት የሚመረጠው የጋራ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ማለት ነው፡፡

1.3.4 አጣሪ ኮሚቴ ማለት በሰነዱ አንቀጽ 16.5 መሰረት የቃል ኪዳን ሰነዱ ተጥሷል የሚል ሰነዱን ፈራሚ ከሆነ ወይም ከሆኑ ፓርቲዎች የሚቀርብ አቤቱታን የሚያጣራና የውሳኔ ሀሳብ የሚሰጥ በጋራ ምክር ቤቱ ለእያንዳንዱ ጉዳይ የሚቋቋም ጊዜያዊ ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

1.3.5 ፓርቲ ማለት መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ.ም ይህን የቃል ኪዳን ሰነድ የፈረመ ፓርቲ ወይም ወደፊት የቃል ኪዳኑን ሰነድ የሚፈርም የፖለቲካ ፓርቲ ማለት ነው፡፡

1.3.6 ኮሚቴዎች ማለት የጋራ ምክር ቤቱ እንደ አስፈላጊነቱ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት በአባላቱ ስራዎቹን ለመስራት የሚያቋቁማቸው ኮሜቴዎች ማለት ነው፡፡

1.4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1.4.1 ይህ ደንብ አቤቱታ በቀረበበት ፓርቲ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

1.4.2 በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሁሉ የሴት ጾታንም ይጨምራል፡፡

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

2. <u>የአቤቱታ አመሰራረት ምርመራ እና ውሳኔ አሰጣጥ</u>

2.1 የቃል ኪዳኑ ሰነድ ላይ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ተጥሰዋል ወይም በቃል ኪዳኑ ሰነድ ላይ የተከለከሉ ሁኔታዎች ተፈጽመዋል ወይም የቃል ኪዳኑን ሰነድ ዓላማ በሚጻረር መልክ እንቅስቃሴ ተደርጓል ብሎ ያመነ ወይም ቅሬታ ያለው ማናቸውም የምክር ቤቱ አባል የሆነ ፓርቲ ቅሬታውን ወይም አቤቱታውን ለጋራ ምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት በጽሑፍ ያቀርባል፡፡

2.2 የምክር ቤቱ ሰብሳቢ፣ ም/ሰብሳቢ እና ዋና ጸሐፊ አቤቱታ ለምክር ቤቱ ለማቅረብ በቂ ምክንያት በጋራ ሲኖራቸው በራሳቸው አነሳሽነት አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

2.3 ከዚህ በላይ በዝርዝር የተገለፀው አቤቱታ አቅራቢዎች ክሱን ወይም አቤቱታውን በጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲሁም አቤቱታውን ያስረዳሉ የተባሉትን ማስረጃዎች አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2.4 ከአቤቱታው ጋር ተያይዘው መቅረብ የሚገባቸው ማስረጃዎች በአቤቱታ አቅራቢው እጅ ከሌሉም ማስረጃዎቹ የሚገኙበትን ቦታ መጥቀስ ይኖርበታል፡፡

2.5 አቤቱታ የሚቀርበው ተቀማጭነቱ በምርጫ ቦርድ በሚሆነው ለምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ነው፡፡

2.6 የምክር ቤቱ ሰብሳቢ አቤቱታ አቤቱታውን ሊመረምር እና የውሳኔ ሀሳብ ሊያቀርብ ለሚችለው ለአጣሪ ኮሚቴ ጉዳዩን ወዲያውኑ ይመራል፡፡

2.7 ጉዳዩን ለመመርመር የተቋቋመው ኮሚቴ ጉዳዩን ማጣራት ይገባል ብሎ ካመነ አቤቱታ የቀረበበት ወገን መልሱን እና ማስረጃዎቹን ማቅረብ እንዲችል አቤቱታው እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡

2.8 አቤቱታው የቀረበበት ፓርቲ ለአቤቱታው መልስ አጣሪ ኮሚቴው በሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2.9 አጣሪ ኮሚቴው ያቀረበውን አቤቱታ፣ የተሰጠውን መልስ እና ማስረጃዎች ከመረመረ በኂላ ጉዳዩን ከግራ ቀኙ በቃል ለመስማት ቀጠሮ ይሰጣል፡፡ በዚህ ቀጠሮ ሁለቱም ወገኖች ቀርበው ጉዳያቸውን ማስረዳት ይኖርባቸዋል፡፡

2.10 አጣሪ ኮሚቴውም ጉዳዩን ከግራ ቀኙ ከሰማ በኂላ የቀረበለትን የጽሑፍ አቤቱታው የቀረበበት ወገን መልስ እና የግራ ቀኙን ማስረጃዎች ከመዘነ በኂላ የውሳኔ ሀሳቡን ለጋራ ምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

2.11 የጋራ ምክር ቤቱ አጣሪ ኮሚቴው ያቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት አድርጎ አለመግባባቶቹ በአስማሚ (Mediators) እንዲፈታ ሃሣብ ለሁለቱም ወገኖች በማቅረብ በመጀመሪያ ጥረት ለማድረግ ማዘዝ ይችላል፡፡

2.12 የቀረበውን አቤቱታ እና ይህንኑ መሰረት ያደረገው የአጣሪ ኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ በአስማሚ ሊፈታ የሚችል አይደለም ብሎ ካመነ ወይም የአግባቢው ጥረት ዋጋ ሳያገኝ ሲቀር የጋራ ምክር ቤቱ ወደ ውሳኔ የመስጠት ስርዓት ሊገባ ይችላል፡፡

2.13 የጋራ ምክር ቤቱ በአጣሪ ኮሚቴው በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ላይ ውሳኔ የሚሰጠው በጠቅላላ ጉባኤው በስምምነት (Consensus) ነው፡፡ ይሁንና የምክር ቤቱ ጉባኤ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻለ በስብሰባው ላይ በተገኙ አባላት ¾ ድምጽ ውሳኔውን ማስተላለፍ ይችላል፡፡

2.14 ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው ጥፋት በተፈፀመ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ አቤቱታው ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

<u>***ምዕራፍ ሶስት***</u>

## 3. <u>የቅጣት ውሳኔ</u>

3.1 ከዚህ በላይ የተገለጹት የማስማማት ጥረቶች ውጤት ሳያመጡ ሲቀሩ ምክር ቤቱ ለአቤቱታው ምክንያት ሆኖ ባገኘው የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ምክር በመስጠት ስህተቱ እንዲታረም፣ እንዲስተካከል የሚያደርግ የማስጠንቀቂያ ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

3.2 አጥፊው አስቀድሞ የተሰጠውን ምክር ለማዳመጥ ፈቃደኛ ሆኖ ከጥፋቱ ካልታቀበ የጋራ ምክር ቤቱ በስብሰባዎች ላይ ድምጽ የመስጠት መብቱን እንዲሁም በተለያዩ ኮሚቴዎች ያለውን ተሳትፎ በግልጽ ለተወሰነ ጊዜ የማገድ የቅጣት ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

3.3 ከላይ በተራ ቁጥር 3.2 በተገለፀው መሠረት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከኮሚቴ ተሳትፎ ለታገደበት ጊዜ ምክር ቤቱ በተለዋጭነት የሚያገለግል ሌላ የኮሚቴ አባል ይሰይማል፡፡

3.4 ምክር ቤቱ ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው ፓርቲ በፈጸመው ጥፋት የቃል ኪዳኑ ሰነድ ተጥሷል ብሎ ካመነ እና ጥፋቱን በመገናኛ ብዙኃን እንዲገለጽ በማድረግ መቅጣት ተገቢ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሰ ይህንኑ የቅጣት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

3.5 ከዚህ በላይ የተገለጹትን ቅጣቶች የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፡፡ አስፈላጊ በሆነ ጊዜም ምክር ቤቱ ለዚሁ ተግባር ጊዜያዊ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

3.6 አንድ የቅጣት ውሳኔ የተሰጠበት ፓርቲ ይህ ውሳኔ እንዲነሳለት ከስድስት ወር በኋላ በድርጊቱ የተጸጸተ መሆኑን በመግለጽ እና ይህንኑ ጸጸቱን ያረመበት ማስረጃ በማቅረብ ውሳኔው እንዲነሳለት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

3.7 ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 3.5 መሠረት ለጋራ ምክር ቤቱ የቅጣት ይነሳልኝ አቤቱታ ሲቀርብ የቀረበውን አቤቱታ በመመርመር ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ምክር ቤቱ ይሰጣል፡፡

3.8 የቅጣቱ ውሳኔ እንዲሁም የግራ ቀኙ የጽሑፍ፣ የቃል ክርክር እና ማስረጃዎች በጋራ ምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት እና በባለጉዳዮቹ ፓርቲዎች ፋይል ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

3.9 የምክር ቤቱን ስብሰባዎች የሚያውኩ ባሕሪያት በምክር ቤቱ አባላት በጉባኤዎች ላይ ሲንፀባረቅ ምክር ቤቱ በቃለ ጉባኤ መዝግቦ ግሣጼ ያደርጋል፡፡ በተደጋጋሚ ስብሰባዎችን የሚያውክ ተግባር በፈፀመ አባልም ምክር ቤቱ ከማስጠንቀቂያ እስከ የተወሰኑ ስብሰባዎችን እንዳይካፈል እንዲሁም በተካፈለው ስብሰባ ላይ ድምፅ የመስጠት መብቱን የማገድ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

3.10 የቅጣት ውሳኔ ቅጂው ለቦርዱ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

ምዕራፍ አራት

## 4. ሚስጥር ስለመጠበቅ

4.1 አንድን አቤቱታ በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ ለመስጠት የተቋቋመ ጊዜአዊ አጣሪ ኮሚቴ አባላት በመታየት ላይ ያለውን ጉዳይ ዝርዝር በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

4.2 አጣሪ ኮሚቴ ለጋራ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ የደረሰበትን የውሳኔ ሀሳብ ከሰጠ በኂላ ምክር ቤቱ ጉዳዩን በአስማሚ ለመፍታት ሙከራ ማድረግ ይገባል ተብሎ ጉዳዩ በአስማሚ እጅ ባለበትም ጊዜ ከጉዳዩ ጋር ዝምድና ወይም ግንኙነት ለሌላቸው ወገኖች ከዚህ በላይ በአንቀጽ 4.1 በተገለጸው መሰረት ማሳወቅ መወያየት አይችልም፡፡

4.3 ጉዳዩ በአስማሚ ወይም በጋራ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ከሆነ ሚስጢራዊነቱ አይጠበቅም፡፡

ምዕራፍ አምስት

## 5. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 5.1 ማሻሻያ

የጋራ ምክርቤቱ ይህን የስነ ሰርዓት ደንብ ማሻሻል ያስፈልጋል ብሎ ባመነ በማናቸው ጊዜ የማሻሻል ስልጣን አለው፡፡ ደንቡም የሚሻሻለው በአባላት ሙሉ ስምምነት ወይም ሙሉ ስምምነት ካልተገኘ በ3/4ኛ ድምጽ ይሆናል፡፡

### 5.2 ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ስማቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የጋራ ምክር ቤቱ አባላት በፊርማቸው ከአጸደቁበት ከዛሬ ሚያዝያ 5 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት | | |
| 2 | የኢትዮጵያ ሰላማዊ የዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 3 | የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 4 | የኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 5 | የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት | | |
| 6 | ገዳ ሥርዓት አራማጅ ፓርቲ | | |
| 7 | የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት | | |
| 8 | መላው ኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 9 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ | | |
| 10 | የመላው ኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ንቅናቄ | | |
| 11 | ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ | | |
| 12 | የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ | | |
| 13 | የወለኔ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 14 | የመላው ኦሮሞ ህዝብ ዲሞክራቲክ ፓርቲ | | |
| 15 | የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ | | |
| 16 | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ | | |
| 17 | ሰማያዊ ፓርቲ | | |
| 18 | የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ | | |
| 19 | አዲስ ትውልድ ፓርቲ | | |
| 20 | የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ | | |
| 21 | አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ | | |
| 22 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ኮንግረስ | | |
| 23 | ምክክር ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ | | |
| 24 | የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ | | |
| 25 | ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ | | |
| 26 | የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 27 | ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 28 | የምዕራብ ሶማሌ ዲሞክራቲክ ፓርቲ | | |
| 29 | የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ | | |
| 30 | የኦሮሞ አቦ ነጻነት ግንባር | | |
| 31 | የደንጣ፣ ዱባሞ ክችንችላ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 32 | የከምባታ ሕዝቦች ኮንግረስ | | |
| 33 | የትግሪ ወርጂ ብሔረሰብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 34 | የኦሮሞ ነጻነት አንድነት ግንባር | | |
| 35 | የዶንጋ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 36 | የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ | | |
| 37 | የኢትዮጵያዊያን አንድነት ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 38 | የኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 39 | የሐድያ ብሔር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 40 | የጌዴኦ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 41 | የየም ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 42 | የአፋር ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 43 | የኦሮሚያ ነጻነት ብሔራዊ ፓርቲ | | |
| 44 | የኦሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት | | |
| 45 | የሲዳማ አርነት ንቅናቄ | | |
| 46 | የወላይታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር | | |
| 47 | የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 48 | ዱቤና ደገኒ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 49 | የዲል ወቢ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 50 | የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር | | |
| 51 | የሲዳማ ሀዲቾ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 52 | የቤንች ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 53 | የሸኮና አካባቢው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 54 | ዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲ ሉዓላዊነት | | |
| 55 | የአርጎባ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 56 | የሐረሪ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 57 | የጋምቤላ ሕዝቦች አንድነት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 58 | የአርጐባ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 59 | የቤንሻንጉልና ጉሙዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 60 | የአገው ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 61 | የጉምዝ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 62 | የቤንሻንጉል ሕዝብ ነፃነት ንቅናቄ ለሠላምና ለዴሞክራሲ ድርጅት | | |
| 63 | የስልጤ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 64 | የደቡብ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኮንግረስ | | |
| 65 | የጋምቤላ ህዝቦች ነፃነት ንቅናቄ | | |
| 66 | የቅማንት ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 67 | ኢትዮጵያዊያን ሀገር አቀፍ ንቅናቄ | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 68 | የኦሮሞ ነፃነት ንቅናቄ | | |
| 69 | የኦሮሚያ ብሔራዊ ፓርቲ | | |
| 70 | የአገው ብሔራዊ ሸንጎ | | |
| 71 | ነፃነት ለአንድነትና ለፍትሕ ፓርቲ | | |
| 72 | የኦሮሞ ነፃነት ግንባር /ኦነግ/ | | |
| 73 | ነፃነትና ሰላም ለኢትዮጵያ ኅብረት ፓርቲ /ሰላም/ | | |
| 74 | የአፋር ሕዝብ ፓርቲ | | |
| 75 | የጋምቤላ ሕዝቦች ፍትህ ለሰላምና ልማት ዲሞክራቲክ ንቅናቄ /ጋህፍሠልዲን/ | | |
| 76 | የአፋር ሕዝብ ነፃነት ፓርቲ /አህነፓ/ | | |
| 77 | ነፀብራቀ አማራ ድርጅት /ነአድ/ | | |
| 78 | የአፋር ሕዝቦች ፍትሐዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 79 | የአፋር ነፃ አውጭ ግንባር ፓርቲ | | |
| 80 | የቁጫ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 81 | ሞቻ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 82 | የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ህብረት /ደምኢህ-ህብረት/ | | |
| 83 | የጋምቤላ ክልላዊ ንቅናቄ | | |
| 84 | የሲዳማ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ /ሲብዴፓ/ | | |
| 85 | አርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ | | |
| 86 | የኢትዮጵያ አረንጓዴ ሊብራል ፓርቲ | | |
| 87 | የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ | | |
| 88 | የኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ንቅናቄ /ኢብን/ | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 89 | የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር /ትዴት/ | | |
| 90 | የአማራ ሕልውና ለኢትዮጵያ አንድነት | | |
| 91 | ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ /ኢትዮጵያችን/ | | |
| 92 | የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር | | |
| 93 | የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር /ኦዴግ/ | | |
| 94 | የኦሮሚያ ነፃነት ዴሞክራሲያዊ ግንባር | | |
| 95 | የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር /ኦብነግ/ | | |
| 96 | ሐረሪ ሪቫይቫል ንቅናቄ | | |
| 97 | የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ | | |
| 98 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሽግግር ም/ቤት /ሽግግር/ | | |
| 99 | የኢትዮጵያ ነፃነት ፓርቲ | | |
| 100 | የኢትዮጵያ መድህን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ /መድህን/ | | |
| 101 | ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ | | |
| 102 | የኢትዮጵያ ኅብረሕዝብ ብሔራዊ ንቅናቄ /ኅብረሕዝብ/ | | |
| 103 | የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 104 | ቱሳ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት /ቱሳ/ | | |
| 105 | ደቡብ አረንጓዴ ኮከብ ኅብረት | | |
| 106 | የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ኅብረት | | |
| 107 | የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት ፓርቲ /ኢሕዴኅፓ/ | | |
| 108 | ብሩህ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ብሩህ/ | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 109 | የኦሮሞ አንድነትና ዴሞክራሲ የፌዴራል የሠላም ለውጥ ፓርቲ | | |
| 110 | የተባበሩት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር | | |
| 111 | የጉራጌ ሕዝባዊ ንቅናቄ | | |
| 112 | አንድነት ለሰላምና ለእኩልነት ዲሞክራሲ ፓርቲ | | |
| 113 | የአዲስ አበባ ሕዝብ ፓርቲ | | |
| 114 | ብሔራዊ ተሀድሶ ለሰላም ልማት | | |
| 115 | የኢትዮጵያ ሪፐብሊካን ፓርቲ | | |
| 116 | የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ንቅናቄ | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |